# በውይይት መድረካችን ላይ አንደራደርም!!

ዮናስ 02-23-17

በገዥው ፓርቲ ኢሕአዴግ የሚመራው የኢፌዲሪ መንግሥት የሕዝብን የከተማቹ ጥያቄዎች ሙሉ ለሙሉ መመለስ አለመቻሉ ለጽንፈኛ ሴራቸው እንደምቹ አጋጣሚ የተጠቀሙበት ሃይሎች በፈጠሩት  ቀውስ የአገር ህልውናን ከመፈታተን ጀምሮ በሰው ህይወትና ንብረት ላይ የሆነውን ሁሉ እናውቀዋለን። እነዚህ ሃይሎች የህዝቡን ጥያቄ ይጠምዝዙት ዘንድ ማስቻሉና የመንግሥት አሠራርን ለሕዝብ ግልጽ ያለማድረግና በአንዳንድ ዘርፎች/ሴክተሮች በህገ መንግስቱ የተደነገገው የተጠያቂነት አሰራር መጣሱ ሁኔታውን ይበልጥ አባባሶት የነበረ መሆኑም እሙን ነው፡፡ ራሳቸውን ከሕግ በላይ ያደረጉ ግለሰቦችና ቡድኖች ሕዝብን ንቀው የነበረ መሆኑም በተመሳሳይ፡፡ ያሳለፍናቸውን ስድስት የሚደርሱ ወራት ያሳለፈውና እየተካሄደ ያለው ጥልቅ ተሃድሶ ውስጥ የተገባው በመንግስትና በመሪ ድርጅቱ በየደረጃው በሚገኙ አመራሮች የተፈጸሙ ጥፋቶች ከሚገመቱት በላይ መሆናቸው ሲሆን፤ እነዚሁ አመራሮችም በየጥልቅ ተሀድሶው መድረክ እና በየመገናኛ ብዙሃኑ የእምነት ክህደት ቃላቸውን ሰጥተው አድምጠን/ተመልክተናል።

የፓርቲና የመንግሥት ሥራን በመቀላቀል ሕገወጥ ተግባራት መፈጸማቸውን፤ በኔትወርክ በመቧደን የሃገር ሀብት ያለቅጥ መዝረፋቸውን፤ የግዥና የጨረታ ሕጎችን እየጣሱ ራስንና ቢጤዎቻቸውን ማበልፀጋቸውን፤ መብታቸውን ለማስከበር እና አገልግሎት ለማግኘት የሚንቀሳቀሱ ዜጎችን ማንገላታታቸውና የመሳሰሉትን መፈጸማቸውን፤ እንዲሁም ይህንኑ በማረም የህዝብን ጥያቄ ለመመለስና የተጀመረውን ልማት ለማስቀጠል እስከህዝቡ ድረስ የወረደ ጥልቅ ተሃድሶ ማስፈለጉን ገዥው ፓርቲ ተናግሮ በየአደባባዩም ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል።

የሃገሪቱ ልማት ባለቤት ሕዝብ መሆን ሲገባው፣ በተለይ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ተቋማትና አመራሮች በጭፍን ሲወስዱት የነበረው የመረረ ዕርምጃ የፈጠረው ቀውስ በእርግጥም ሊታረም የሚችለው በጥልቅ ተሃድሶ መድረኮች መሆኑ አያጠያይቅም። በማዘጋጃ ቤቶችና በተለያዩ የአገልግሎት መስጫ ተቋማት የዜግነት መብታቸው ተገፎ ለእንግልት የተዳረጉና በገንዘባቸው ፍትሕ እንዲገዙ ለተገደዱ ዜጎች እነዚህ መድረኮች ወሳኝ መሆናቸው

አያከራክርም፡፡ ሕዝብና መንግሥትን ያጋጩ መሰል ጉዳዮችም መፍትሄ ያገኙ ዘንድ የእነዚህ መድረኮች ፋይዳ አሌ አይባልም። በመሆኑም ሕዝብ ለመንግሥት ያቀረባቸው በርካታ ጥያቄዎች አሉት፡፡ ቅደም ተከተላቸው ተጠብቆ የቀረቡት ጥያቄዎች በአግባቡ ምላሽ ያስፈልጋቸዋል፡፡ ከዚህ ቀደም በተደጋጋሚ የቀረቡ አቤቱታዎች ሰሚ አለማግኘታቸው ለጽንፈኛ ሃይሎች በፈጠረላቸው ቀዳዳ በሃገሪቱ ላይ ተከስቶ የነበረው ቁስል ግና አላጠገገም፡፡ ሕዝብና መንግሥት ሆድና ጀርባ ሆነው ሊደማመጡ ባለመቻላቸው የበርካቶች ሕይወት ተቀጥፏል፤ በርካቶች ለአካል ጉዳት ተዳርገዋል፤ መጠኑ ከፍተኛ የሆነ የአገር ሀብት ወድሟል፤ በብዙዎች ላይ ከፍተኛ የሆነ የሥነ ልቦና ቀውስ ተፈጥሯል፡፡ የአገርና የሕዝብ ህልውና ለአደጋ ተጋልጠ የነበረ መሆኑም የማይዘነጋ፣ ገና ያልጠገገ ስጋት ነው ፡፡

በእርግጥ በተፈጠረው ቀውስ ምክንያት የስድስት ወራት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ታውጆ ችግሮችን ማርገብ ተችሏል። ያም ሆኖ ግን ለዘላቂ ሰላም የሚበጁ ሃገራዊ ጉዳዮች ላይ በጋራ በመምከር ሁነኛ መፍትሔ መሆኑን በማመን የጥልቅ ተሃድሶ መድረኮችን አዘጋጅቶ መምከሩ ተገቢና ዴሞክራሲያዊ ስርአትን እየገነባሁ ነው ከሚል መንግስት የሚጠበቅ ነው፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ ለዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታው ሚናቸው የማይናቅና ምናልባትም ከገዥው ፓርቲዎች እንደሚተካከል ከማያጠያይቁት ተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋር መደራደርንም የጥልቅ ተሃድሶው አካል ማድረጉ በእርግጥም ገዥው ፓርቲ ለዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ የሚተጋ ለመሆኑ ሁነኛ ማሳያ ነው።

ባለፉት 25 ዓመታት፣ በኢህአዴግ አመራር በሰላማዊ ፖለቲካዊ ምኅዳር ውስጥ በርካታ ውጣ ውረዶች የታለፉ መሆናቸው ይታወቃል፡፡ በተለይ ከዜሮ በታች የነበረው የሃገሪቱ ኢኮኖሚ ከማጥ ውስጥ ተነስቶ በርካታ ተስፋ ሰጪ ውጤቶችን አሳይቷል፡፡ በተለይ በትምህርትና በጤና ዘርፍ አመርቂ ሥራዎች ተሠርተዋል፡፡ ነገር ግን ሕዝብ በገዛ አገሩ የባይተዋርነት ስሜት እየተሰማው፣ ከዝቅተኛው እስከ ከፍተኛው ሹም ድረስ ግልምጫ እየደረሰበት፣ በየደረሰበት ቦታ ሁሉ ጉቦ እንዲከፍል መገደዱ ሳያንስ የአገልግሎት መስተጓጎል ወይም መቋረጥ ሲያጋጥመው እንኳን ይቅርታ የሚጠይቀው አካል እንኳ ያልነበረ መሆኑ ሲታሰብ በርግጥም ጉዳዩ ያስደነግጣል። ይህ ሁሉ ይወገድ ዘንድ የጥልቅ ተሀድሶው አስፈላጊነት በምንም መንገድ አጠያያቂ አይሆንም።

ምንም እንኳን በጥልቅ ተሀድሶው በርካታ ችግሮች እየተቀረፉ ቢሆንም፤ በጥልቅ ተሃድሶው ሁሉም ነገር በሰላም የተጠናቀቀ ያህል እየተነገረ መሆኑ ላይ ይህ ጸሃፊ አይስማማም፡፡ አሁንም ህዝብ ነቅሶ ያላወጣቸውና ሆን ብለው የተደበቁ፤ ሀይለኛው ንፋስ እስኪያልፍ ልክ እንደሰንበሌጡ ለሽ ያሉ ብልጣ ብልጦች መኖራቸው በደማቁ ሊሰመርበት ይገባል።

በእርግጥ ሁሉም ችግሮች በአንድ ጊዜ መፍትሔ አያገኙም፤ ባንዴ ሁሉም ጥያቄዎች ምላሽ ሊገኝላቸው አይችልም፡፡ ነገር ግን በጣም መሠረታዊ የሚባሉ ጥያቄዎች ግን ምላሽ ያስፈልጋቸዋል፡፡ ስለሆነም እፎይ ብለን የምንቀመጥበት ሰአት ላይ እንዳልደረስን ተገንዝበን ሁላችንም በየፊናችን የየድርሻችንን ልንወጣ ይገባል። በተለይ በፓርቲዎቹ መካከል የሚደረገው ድርድር ላይ ተሳትፏችን የበዛ ሊሆን የግድ ነው። ምክንያቱ ደግሞ ግና ከጅምሩ ጭንጋፍ ምልክታዎች እየተንጸባረቁ ይገኛሉና። ዴሞክራሲ ሥርዓት ሆኖ እንዲቀጥል ሃላፊነቱ የመንግሥት ወይም የገዥው ፓርቲ ብቻ እንዳልሆነ ስለድርድሩ ስኬት ህዝቡ ሊገነዘብ ይገባል፡፡ በሰላማዊ የፖለቲካ ትግሉ ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ ኃይሎችን ሁሉ እገዛ ይፈልጋል፡፡ የፖለቲካ ፓርቲ እንደ ሱቅ በደረቴ መሥርቶ አለሁ በማለት የተበታተነ ትግል ከመምራት ይልቅ፣ በርዕዮተ-ዓለምና በዓላማ እንግባባለን የሚሉ ተሰባስበው ጠንካራ ድርጅት መፍጠር ይገባቸው ዘንዳ ህዝብ ይወክለኛል በሚለው ላይ ሁሉ ግፊት ማድረግ ይገባዋል፡፡

በብሔራዊም ይሁን በህብረ ብሔራዊ አደረጃጀት ውስጥ ሆነው በምርጫ ጊዜ ብቻ ከያሉበት እየተጠራሩ በመምጣት “ምኅዳሩ ጠበበብን” የሚሉትን አጣባቢዎች በቃችሁ ሊላቸው ይገባል። የተለያዩ የሃገር ውስጥ መገናኛ ብዙሃኖች ዘገባ የሚያመላክተውም ይህንን ድርድር ለማጨንገፍ እየተጉ የሚገኙት እነዚሁ አጣባቢ ሃይሎች መሆናቸውን ነው። ከገዥው ፓርቲ ጋር ለመደራደርም ሆነ ለመፎካከር የሚቻለው ከብዛት ይልቅ ጥራት ሲኖር እና ለዴሞክራሲያዊ ውይይቶች ክፍት መሆን ሲቻል ብቻ ነው፡፡

በግለሰቦች ተክለ ሰውነት ሥር የተከለሉ፣ አባላቶቻቸውም ሆኑ ደጋፊዎቻቸው የማይታወቁ መናኛ ፓርቲዎች ለአገር የሚፈይዱት ምንም ነገር የለም፡፡ ከዘመኑ አስተሳሰብ ጋርም አይሄዱም፡፡ በድርድር የማመቻመቻ መድረኩም የታየው ይህ እና ከላይ በተመለከተው ዓይነት ተደራጅተው የተለመደ አሰልቺ ሁኔታ ውስጥ ለመዘፈቅ የሚባትሉ ሃይሎች ናቸው፡፡

ባሳለፍናቸው 5 የሚደርሱ ሃገር አቀፍ ምርጫዎች ላይ ያየናቸውና የሚበዙት የተቃውሞው ፖለቲካ ስብስቦች የፖለቲካ ባህል ኋላቀር፣ ከሥልጣኔ ጋር የማይተዋወቅ፣ ለሰጥቶ መቀበል መርህ ቦታ የማይሰጥ፣ በጭፍን ጥላቻ የተዋጠ፣ ከውይይትና ከድርድር ይልቅ እልህና ጉልበት የሚበረታበት፣ በሸፍጥና በሴራ የተተበተበ፣ ቡድንተኝነት የሚያጠቃው ነው። ወይ ጠቅልሎ የመውሰድ አለበለዚያም በዜሮ የመውጣት አባዜ የተጠናወተው የነዚህ ሃይሎችን (የመስቀል ወፍ ፖለቲካም እንኳ ቢሆን) ያለፈ ታሪክ ስንመረምር ዴሞክራሲ የሚል ታፔላ ቢለጠፉም፣ ውስጣቸው ግን ጸረ-ዴሞክራሲያዊ መሆኑን መገንዘብ አያቅትም፡፡ እንዲህ አይነት ፖለቲካ ደግሞ ትውልዱን የማይመጥን እና ዳግመኛ እድል ሊሰጠው የማይገባ ነው።

ከጊዜያዊ ኅብረት ምሥረታ እስከ ግንባርና ውህደት ድረስ በታዩ ውጣ ውረዶች፣ የጋራ አማካይ ፈጥሮና ልዩነትን አስታርቆ መሥራት ሲያቅተው በተደጋጋሚ የተመለከትነው ይህ ስብስብ ዛሬም ድርድሩን እንዲያጨነግፍ እድል ሊሰጠው አይገባም፡፡ ይህ የተበላሸ የፖለቲካ ባህል ሥር ነቀል ለውጥ ያስፈልገዋል፡፡

እነዚህ ሃይሎች ዴሞክራሲ የሚባለው ጽንሰ ሐሳብ ትርጉሙ ግራ እስከሚያጋባ ድረስ ፈሩን እንዲስት ማድረጋቸው፤ ይልቁንም ጽንፈኝነትና ጭፍንነት የበላይነት እንዲያገኙና ሰላም እንዲደፈርስ ምክንያት መሆናቸው ሊዘነጋ አይገባም፡፡ ይህ ስብስብ ሕገወጥነት ስለተፀናወተው ለሕግ የበላይነት ክብር ነፍጓል፡፡ የአገር ጉዳይ ያገባናል የሚሉ ዜጎች ላይ ታፔላ በመለጠፍ ድምፃቸው እንዲታፈን አድርጓል፡፡ ሕግ ባለበት አገር ሕገወጥነት እንዲሰፍን እና ከላይ በተመለከተው መልኩም ውጤቱ አስከፊ እንዲሆን ምክንያት የነበረ መሆኑን ስለድርድሩ ስኬት ባለቤት የሆነው ህዝብ በሚገባ ሊያስታውሰው ይገባል፡፡

የኢሕአዴግና የተቃዋሚዎች ድርድር ብልሹውን የፖለቲካ ባህል እንዲያስወግድ ከተፈለገ፣ ሰከን ያለና የሠለጠነ ግንኙነት እንጂ የቀደመው የቡድንተኝነት እና የድርቅና ፖለቲካ አያስፈልገንም፡፡ ዴሞክራሲ ሐሳቦች በነፃነት የሚሸንሸራሸሩበት፣ የማያስማሙ ጉዳዮችን እያቻቻሉ በሚያስማሙ ጉዳዮች ላይ የሚግባቡበት፣ ከኃይል ይልቅ ውይይትን የሚያስቀድሙበትና ለሕዝብ ፍላጎት ተገዥ የሚሆኑበት ነጻ መድረክ እንጂ ጉልበተኞች የሚፈነጩበትና አላዋቂዎች የሚቀልዱበት መድረክ አይደለም፡፡ ሕዝብ ያለምንም መሸማቀቅና ፍራቻ ተወካዮቹን በነፃነት የሚመርጥበት ሥርዓት በመሆኑ፣ የፖለቲካ

ፓርቲዎች በእኩል ሜዳ ላይ በነፃነት ሊወዳደሩ ዝግጁ መሆናቸው የሚረጋገጠው ለእንዲህ አይነት የውይይት መድረኮች ባላቸው ቀናኢነትና ስልጡንነት መሆኑንም ባለቤት የሆነው ህዝብ ስለድርድሩ ስኬት አጥብቆ ሊያጤን ይገባል፡፡ ስለሆነም የድርድሩ ተሳታፊ የሆኑ ሁሉም ፓርቲዎች ለእርስ በርስ ዕውቅና መሰጣጣትና ለሰጥቶ መቀበል መርህ ተገዥ ሊሆኑ የግድ ነው፡፡ ይህ በንድፈ ሐሳብ ደረጃ የሚንፀባረቅ ፍላጎት መሬት ላይ ወርዶ በተግባር እንዲታይ፣ እነዚህ ሃይሎች መጀመሪያ ለሕግ የበላይነት መገዛት አለባቸው፡፡ ዴሞክራሲ በሕግ የበላይነት ሥር የሚመራ መንግሥታዊ ሥርዓት ነውና፡፡

ውይይትም ሆነ ድርድር ለማድረግ በዝግጅት ላይ የሚገኙት ሁለቱ ወገኖች ለህዝብ የሚጠቅሙት ያለፉትን ቂምና ቁርሾዎች ወደ ጎን በማድረግና ለአገርና ለሕዝብ ምንም ጥቅም እንደሌላቸው ከልብ በማመን፣ አዲሱን ጉዞ በሠለጠነ መንገድ ላይ በመጓዝ ሲጀምሩት እንጂ፤ የታሰሩ ይፈቱ፣ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ይነሳ ወዘተ የሚሉ ህዝብን ያላማከሉ ጩኸቶችን በማሰማት አይደለም፡፡ ነጋ ጠባ ጠበበ የሚሉት የፖለቲካ ምኅዳር ጠቦ ከነበረ እንኳ መስፋት የሚችለው እና  ሁሉም የአገሪቱ ፓርቲዎች በእኩልነትና በነፃነት እንዲፎካከሩ ማድረግ የሚቻለው በእንደዚህ አይነት የውይይት መድረኮች መሆኑን ታሳቢ ያደረገ ትዝብትና ውሳኔም ከህዝብ ይጠበቃል። ከፖለቲካ ፍጆታነት የማይዘሉ አጓጉል ድርጊቶችን በማስወገድ የዜጎችን አንገት ሲያስደፉ የኖረውን አስከፊ የፖለቲካ ባህል መለወጥ ጊዜው አሁን ነው፡፡ ድርድሩም ሆነ ውይይቱ በቀና መንፈስ እንዲጀመር ሲፈለግ በቅድመ ሁኔታዎች እያመካኙ ምክንያት መደርደር ሊቆም ይገባል፡፡ ድርድሩም ሆነ ውይይቱ ለሰጥቶ መቀበል መርህ ክፍት ከሆነ ቀዳሚው ጉዳይ የአገርና የሕዝብ ጥቅም ይሆናል፡፡ ለዚህ ደግሞ ቁጠርኛ መሆን ግዴታ ነው፡፡

በየደረጃው የተደረገውና እየተደረገ የሚገኘው ጥልቅ ተሃድሶ ስኬታማ ሆኖ ሁሉአቀፍ በሆነ መልክ የህዝቡን ጥያቄ ሊመልስ የሚችለውና የተጀመረውን ልማት በማስቀጠል ሃገሪቱን ወደበለጸጉት ጎራ መቀላቀል የሚቻለው የነዚህ ሃይሎች ያልተቋረጠና ምክንያታዊ ተሳትፎ ሲኖር ብቻ ነው። ስለሆነም የጥልቅ ተሃድሶው መቋጫ እንደሚሆን ለመገመት በማያዳግተው ድርድር ላይ የሚያፌዙትን በለመዱት መንገድ ልንደራደራቸው አይገባም። ይልቁንም እነሱ በለመዱትና በወደዱት፣ ከላይ በተመለከተ መንገድ ላለመደራደር የሚያስችሉንን አይነት መረጃዎችና አዝማሚያዎች ልንቃርምና በቅርብ ሆነን ልንከታተል ይገባል።